በአራዳ ክ/ከተማ ወረዳ 4 ት/ ጽ /ቤት አዜ ፋሲል ክላስተር ማዕከል በ 2015 ዓ.ም የሁለተኛ መንፈቀ ዓመት ማጠቃለያ የ 6 ተኛ ክፍል የአካባቢ ሳይንስ ት/ት ሞዴል ፈተና

የተፈቀደ ጊዜ 1፡30

አጠቃላይ መመሪያ

ይህ ፈተና በአጠቃላይ 40 ጥያቄዎችን የያዘ ሲሆን እያንዳንዱ ጥያቄና የተሰጡ የመልስ አማራጮችን በጥንቃቄ ካነበባቹ በኃላ ትክክለኛ መልስ የሆነውን በመምረጥ በተሰጠው የመልስ መስጫ ወረቀት ላይ በመረጣችሁት ፊደል ሥር የተቀመጠውን የማጥቆሪያ ቦታ በእርሳስ በማጥቆር መልስ ስጡ ።

_____1. ከሚከተሉት ውስጥ የአንጻራዊ መገኛ የማነጻጸሪያ ነጥብ ያልሆነው የቱ ነው ?

ሀ. ውሃማ አካላት ሐ. ሀገራት

ለ. ተራሮች መ. የዲግሪ ልኬት

_____2. ስለ ኬንትሮስ ማዕዘናዊ መለኪያ ትክክል የሆነው ሀሳብ የቱ ነው ?

ሀ. በካርታ ላይ ከምዕራብ ወደ ምሥራቅ ተሰምረው ይገኛሉ

ለ. በምዕራብ እና በምሥራቅ ያሉ ቦታዎችን በዲግሪ ይገልጻሉ

ሐ. የኬንትሮስ መስመሮች አግድም ይሰመራሉ

መ. ለምድር ወገብ የዲግሪ ልኬት መነሻ ነው


_____3. ከዐበይት ትይይዩ መስመሮች ውስጥ የካንሰር መስመር የሚገኘው በስንት ዲግሪ ላይ ነው ?

ሀ. $23^0\frac{1}{2}$ ሰሜን ሐ. $23^0\frac{1}{2}$ ደቡብ

ለ. $66^0\frac{1}{2}$ ሰሜን መ. $66^0\frac{1}{2}$ ደቡብ

_____4. የሚከተሉትን አግድም እና ቁቅሚ መስመሮች በመመልከት የፊደል " ለ" መገኛ በዲግሪ ልኬት ስንት ነው ?

ሀ. 0^0 ሰሜን ኬክሮስ እና 0^0 ኬንትሮስ ሐ. 5^0ሰሜን ኬክሮስ እና 10^0ደቡብ ኬንትሮስ



ለ. 10^0 ሰሜን ኬክሮስ እና 20^0 ምዕራብ ኬንትሮስ መ. 5 ዲ ምዕራብ ኬክሮስ እና 10 ዲ ደቡብ ኬንትሮስ

_____5. ከሚከተሉት ውስጥ የምስራቅ አፍሪካን ከሚያዋስኑ ውሃማ አካላት መካከል ትልቁ__ ነው ?

ሀ. የቀይ ባህር ሐ. የህንድ ውቅያኖስ

ለ. የኤደን ባህረ ሰላጤ መ. የአትላንቲክ ውቅያኖስ

_____6. ከምሥራቅ አፍሪካ ቀንድ ሀገራት ውስጥ የማትካተተዋ ሀገር ማን ናት ?

ሀ. ኢትዮጵያ ሐ. ኤርትራ

ለ. ኬንያ መ .ጅቡቲ

_____7 የራስ ደጀን ተራራ መገኛ እና ከፍታ ሜትርን በትክክል የሚገልጸው የቱ ነው ?

ሀ. ዩጋንዳ - 4321 ሐ. ኢትዮጵያ - 4620

ለ. ታንዛኒያ - 5895 መ. ኬንያ - 5200

_____8. _____ተግባራቸው ሰውነት ሲደማ ብዙ ደም እንዳይፈስ ለማርጋት ይጠቅማሉ።

ሀ. ቀይ የደም ሕዋስ ሐ. ነጭ የደም ሕዋስ

ለ. ፕላዝማ መ. ፕሌትሌቶች

_____9. ደምን ከተለያዩ የሰውነት ክፍሎች ተቀብሎ ወደ ልብ የሚያደርሰው የደም ሥር አይነት የቱ ነው ?

ሀ. ደም ቅዳ ለ. ደም መልስ ሐ. ቀጫጭን የደም ሥሮች መ. ፕሊትሌቶች

_____10 .የልብ ትርታን የምናዳምጥበት መሳሪያ ምን ተብሎ ይጠራል ?

ሀ . ማይክሮስኮፕ ለ . ቴሌስኮፕ ሐ . ስቴቶስኮፕ መ . መልሱ አልተሰጠም

_____11. ከሚከተሉት ውስጥ በሴቶች ላይ የሚታይ አካላዊ ለውጥ የቱ ነው ?

ሀ. የድምጽ መጎርነን ሐ. የደረት መስፋት

ለ. የዳሌ መስፋት መ . በፊት ላይ ፀጉር መብቀል

_____12. ወደ ውስጥ ስንተነፍስ አየር ወደ ሳንባችን ለመድረስ የሚያልፍባቸው የመተንፈሻ አካላት በቅደም ተከተል የሚገልፀው የቱ ነው ?

ሀ . አፍ--ድህረአፍ--- ሰርን---ዐብይ ትንሿ---ተገንጣይ የአየር ቧንቧ---ደቂቅ ትንሿ---ትንከረት

ለ . የአፍንጫ ቀዳዳ ---ሰርን---ድህረአፍ---ዐብይ ትንሿ----ተገንጣይ የአየር ቧንቧ --ደቂቅ ትንሿ --- የአየር ከረጢት

ሐ . ትንከረት----ደቂቅ ትንሿ ----ባላ ትንሿ-----ዐብይ ትንሿ ----- ድህረ አፍ ----ሰርን ----አፍ

መ . የአፍጫ ቀዳዳ -- ሰርን----ድህረ አፍ---- ዐብይ ትንሿ ----ደቂቅ ትንሿ-----ተገንጣይ የአየር ቧንቧ----የአየር ከረጢ

_____13. አየር እና ምግብ በጋራ የሚተላለፍበት የመተንፈሻ አካል የቱ ነው?

ሀ. ድህረ አፍ ለ. ባላ ትንሿ ሐ. ተገንጣይ ቧንቧ መ. የአፍንጫ ቀዳዳ

_____14. አየር ምን አይነት ድብልቅ ነው?

ሀ. ዋህድ-ዘር ድብልቅ ሐ. ሀ እና ለ

ለ. ልዩ-ዘር ድብልቅ መ. ድብልቅ አይደለም

_____15. የናፍጣ እና የውሃ ድብልቅ በየትኛው የመለያ ዘዴ በቀላሉ መለየት ይቻላል?

ሀ. በጥሊያ ለ. በቀረራ ሐ. ትነት መ. በንጥረት

_____16. የሚሙ ጠጣሮችን ከአሚሚው ፈሳሽ የምንለይበት ዘዴ ምን ይባላል?

ሀ. ንጥረት ለ ትነት ሐ. ቀረራ መ. ጥሊያ

_____17. ከሚከተሉት ታዳሽ የጉልበት ምንጮች ውስጥ የማይካተተው የቱ ነው?

ሀ. ውሃ ለ. ንፋስ ሐ. የፀሃይ ብርሀን መ. የተፈጥሮ ዘይት

_____18. በርሜል ሙሉ ዘይት ወይም ነዳጅ መኪና ላይ ለመጫን የሚጠቅመው የቀላል መኪና አይነት የቱ ነው?

ሀ. ሽብልቅ ለ. መፍቻ ሐ. ዘንባይ ወለል መ. መፈንቅል

_____19. በደቂቃዎች በሰዓታት የሚቀያየር የአየር ጠባይ .....ይባላል።

ሀ. የአየር ግፊት ለ. የአየር ሁኔታ ሐ. የአየር ንብረት መ. እርጥበት

_____20. ከሚከተሉት ውስጥ የአየር ንብረት ተቆጣጣሪ ያልሆነው የቱ ነው?

ሀ. ከፍታ ለ. የውቅያኖስ ሞገድ ሐ. የአየር ግፊት መ. ከባህር ያለው ርቀት

_____21. ከሚከተሉት አማራጮች ውስጥ በሩዋንዳና በቡሩንዲ የሚገኝ የማዕድን አይነት የቱ ነው?

ሀ. ግራፋይት እና ጀሶ ለ. የተፈጥሮ ነዳጅና ብረት

ሐ. ሶዳአሽና የሽክላ አፈር መ. ወርቅና ቆርቆሮ

_____22. ካምቢሶል እና ላቪሶል የተባሉት የአፈር አይነቶች በየትኛው የምስራቅ አፍሪካ ሀገር ይገኛሉ?

ሀ. ኬንያ ለ. ሶማልያ ሐ. ኢትዮጵያ መ. ሩዋንዳ

_____23. ዕፅዋት ባልነበረበት ስፍራ ችግኞችን የመትከል ተግባር ምን ይባላል?

ሀ. ድንና ለ. ዳግም ድንና ሐ. ዘር ማፈራረቅ መ. የእርከን ስራ

_____24. የዛምቤዚ ወንዝ ላይ የተሰራው ሰው ሰራሽ ግድብ የትኛው ነው?

ሀ. ቆቃ ለ. ካቦራባሳ ሐ. ካሪባ መ. ለ እና ሐ

_____25. ከሚከተሉት ወንዞች ውስጥ ከኢትዮጵያ የማይወጣው ወንዝ የቱ ነው?

ሀ. ገናሌ ለ. ዋቢ ሸበሌ ሐ. ናይል መ. አዋሽ

_____26. ቅጠለ ሰፋፊ ዛፎች ደን ውስጥ የሚበቅሉ የዛፍ አይነቶች የትኞቹ ናቸው?

ሀ. ቀረሮና ዶቅማ ለ. ሾላና ዋርካ ሐ. ቁልቋልና ግራር መ. ጥድ

_____27. ከማዕከላዊ አፍሪካ ሀገራት መካከል የምስራቅ አፍሪካን ቀጠና የሚያዋስነው የቱ ነው?

ሀ. አንጎላ ለ. ሱዳን ሐ. ቦትስዋና መ. ደቡብ አፍሪካ

_____28. ከምስራቅ አፍሪካ ሀገራት መካከል በህዝብ ብዛት አነስተኛ ቁጥር ያላት ሀገር ማን ናት?

ሀ. ኢትዮጵያ ለ. ማዳጋስካር ሐ. ኤርትራ መ. ሲሼልስ

_____29. ሰዎች በተለያዩ ስፍራዎች ሰፍረው የሚገኙበትን ሁኔታ የሚገልጽ የህዝብ ባህሪያት መገለጫ የቱ ነው?

ሀ. የህዝብ ብዛት ለ. የህዝብ እድገት ምጣኔ

ሐ. የህዝብ ስርጭት መ. የጾታና የእድሜ ቅንብር

_____30. የኩሽ መንግስት የመጀመሪያው ዋና ከተማ ማን ነበር?

ሀ. ሜሮይ ለ. ናፓታ ሐ. አክሱም መ. አዱሊስ

_____31. በአክሱም ከነገሱ ነገስታ መካከል ሜሮይን የወረረው ማን ነው?

ሀ. ንጉስ ኢዛና ለ. ንጉስ ካሌብ ሐ. ንጉስ ዳዊት መ. ንግስት ማክዳ

_____32. ለኑቢያ ስልጣኔ መዳከም ዋናው ምክንያት ምን ነበር?

ሀ. የእርስ በዕርስ ጦርነት ለ. የድርቅ መከሰት

ሐ. የአክሱም ስልጣኔ መነሳት መ. የተፈጥሮ አደጋ

_____33. ትልቁ የጥያ ትክል ድንጋይ ቁመቱ ስንት ሜትር ነው?

ሀ. 37 ሜ ለ. 3.7 ሜ ሐ. 27 ሜ መ. 2.7 ሜ

_____34. የኢጋድ ድርጅት መቀመጫ ሀገር የት ነው?

ሀ. ኤርትራ ለ. ኢትዮጵያ ሐ. ጅቡቲ መ. ታንዛንያ

_____35. የምስራቅ አፍሪካ ማህበረሰብ ድርጅት እ.ኤ.አ መች ተቋቋመ?

ሀ. በ 1999 ዓ/ም ለ. 1986 ዓ/ም ሐ. 1998 ዓ/ም መ. 1991 ዓ/ም

_____36 . ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ የሚያጠቃው የደም ህዋስ የቱ ነው ?

ሀ . ነጭ የደም ህዋስ ለ . ቀይ የደም ህዋስ ሐ . ፕሌትሌቶች መ . ፕላዝማ

_____37. ለኤችአይቪ ኤድስ መተላለፊያ መንገድ ምክንያት የማይሆነው የቱ ነው?

ሀ. ልቅ የሆነ የግብረ ስጋ ግንኙነት

ለ. በእርግዝና ወቅት ከእናት ወደ ልጅ

ሐ. ያልተመረመረ የደም ልገሳ

መ. ስለታም ነገሮችን በግል መጠቀም

_____38. ከሚከተሉት አደንዛዥ እፆች ውስጥ ኒኮቲን የተባለ ኬሚካል የያዘው የቱ ነው?

ሀ. ሲጋራ ለ. አልኮል ሐ. ጫት መ. ሀሺሽ

_____39. ከሚከተሉት አንዱ ጎጂ ልማዳዊ ድርጊት አይደለም?

ሀ. የሴት ልጅ ግርዛት ለ. የለድሜ ጋብቻ

ሐ. ጠለፋ መ. መልሱ አልተሰጠም

_____40. _____ባልተለመደ ሁኔታ የዝናብ እጥረት ሲከሰት የሚፈጠር የተፈጥሮ ክስተት ነው?

ሀ. ረሀብ ለ. ድርቅ ሐ.ስደት መ. ጦርነት